# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በትምህርት ሚኒስቴር
## የዩኒቨርስቲ አቅም ግንባታ ኘሮግራም
## የአሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ
## ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሰኔ/2002

**ማውጫ**

**ርዕስ**

ገጽ

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት** ........ **1**

**ማውጫ** ........ **2**

**ክፍል አንድ** ........ **1**

*መግቢያ* ........ 1
በመገንባት ላይ ያሉት አስራ ሶስት ዩኒቨርሰቲዎች የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /PROCESS DESCRIPTION/........ 2

**ክፍል ሁለት** ........ **6**

*ግኝቶች* ........ 6
*የዩኒቨርስቲዎቹ የፕሮጀክት ቀረፃና እቅድ አፈፃፀም* ........ *6*
*የአዋጪነት ጥናት ስለ አለመከናወኑ* ........ *6*
*የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶችና ኃላፊዎች በእቅድ-ዝግጅት ላይ ስለነበራቸው ተሳትፎ* ........ *7*
*የኃይል ፣ የውሃ አቅርቦት እና ቴሌኮሙኒኬሽንን በተመለከተ ስለተደረገ ዝግጅት* ........ *7*
*ስለ ተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻዎች ዲዛይን* ........ *8*
*ስለግንባታ ዲዛይን ለውጥ፣* ........ *9*
*የዩኒቨርስቲው ግንባታ የአፈፃፀምና የክትትል ስርአት* ........ *10*
*ስለ የፕሮጀክት ማኔጀሮች ምደባ* ........ *10*
*ስለግንባታው ጊዜ* ........ *11*
*ከተማሪ ቅበላ በፊት መከናወን ስለነበረባቸው ስራዎች* ........ *12*
*የመረጃ አያያዝና ክትትል ስርአት* ........ *14*
*የግንባታውን ወጪ በተሟላ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ያለመኖሩ* ........ *14*
*በህንፃዎች ላይ ስለደረሱ ጉዳቶች* ........ *14*
*ስለዕቃ ግዥ* ........ *15*

**ክፍል ሦስት** ........ **17**

*መደምደሚያ* ........ 17

**ክፍል አራት** ........ **19**

*የማሻሻያ ሃሳቦች* ........ 19

አባሪ

አባሪ 1 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች........ i

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. መንግስት በሀገሪቱ ያለውን የትምህርት ሽፋን ለማስፋፋት እና በገጠርና ኋላቀር በሆኑ ክልሎች እንዲሁም ለሴቶች ጥራት ያለው ትምህርት ለማዳረስ፣ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀ ግብር Educational Sector Development Program (ESDP) ቀርጿል፡፡ በዚህም መሠረት የመጀመሪያው ደረጃ (Phase) የሆነው የፕሮግራሙ ክፍል (ESDP I) (1990-1994) ሁለተኛው ደረጃ (Phase) (ESDP II) (1995-1997) እና ሶስተኛው ደረጃ (Phase) (ESDP III) (1998-2002) ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

2. በከፍተኛ ትምህርት ማስፋፊያ የዩኒቨርሲቲዎችን ግንባታ በተመለከተ እስከ

   (ESDP II) መጨረሻ ድረስ ስምንት አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ተቋቁመዋል የቀድሞዎቹን ዩኒቨርስቲዎችንም የማጠናከር ሥራ ተከናውኗል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በሀገሪቱ ባሉ የተለያዩ ክልሎች የማስፋፋትና የማጠናከሩ ስራ አስፈላጊነት የታመነበት በመሆኑ በትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር (ESDP III) የከፍተኛ ትምህርት ተkሚትን የማስፋፊያና የማጠናከሪያ ንዑስ መርሃ ግብር የዩኒቨርሲቲ አቅም ግንባታ ፕሮግራም University Capacity Building Program (UCBP) በአቅም ግንባታ ሚ/ር እና በትምህርት ሚ/ር በጋራ የሚሰራ ፕሮግራም ተቀርጿል::

3. የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማ አስራ ሶስት ዩኒቨርስቲዎችን በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ በአስራ አምስት ከተሞች ማለትም በዲላ፣ በሶዶ፣ ሚዛን ተፈሪ እና ቴፒ፣ በነቀምቴ፣ በድሬዳዋ፣ በጅጅጋ፣ በደሴ እና ኮምቦልቻ፣ በሰመራ፣ በደብረማርቆስ፣ በደብረብርሃን፣ በሮቤ፣ በአክሱም እና በአዳማ በፍጥነትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለመገንባት ነበር፡፡

4. ለግንባታው ጂ.ቲ.ዜድ. በመባል የሚታወቀው የጀርመን የልማት ድርጅት የፕሮጀክቱ ሥራ የአመራርና የአፈጻፀም ወኪል (Project Management and Implementation Agent) እንዲሆን ተመርጧል፡፡ በውሉ መሠረት የግንባታ

ሥራው እንዲጠናቀቅ የታሰበው ከነሐሴ 1997 እስከ መስከረም 2002 ሲሆን፣ ከመስከረም 2002 እስከ መስከረም 2003 ድረስ ያለው አንድ ዓመት ደግሞ የዋስትና ጊዜ ነው፡፡ የአስራ ሶስቱ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ሲጠናቀቅ እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ከ6,000 እስከ 10,000 በጠቅላላው አስራሶስቱም ዩኒቨርስቲዎች እስከ 121,000 ተማሪዎች የመቀበል አቅም እንደሚኖራቸው ተገምቷል፡፡

## በመገንባት ላይ ያሉት አስራ ሶስት ዩኒቨርስቲዎች የአሰራር ሥርዓት መግለጫ /Process Description/

<u>የፕሮጀክቱ አስተዳደር ክትትልና ግምገማ</u>

5. ጂ.ቲ.ዜድ. የኘሮጀክቱ ሥራ አመራርና አፈጻፀም ወኪል (Project Management and Implementation Agent) ሲሆን ጂ.ቲ.ዜድ. የሚቆጣጠራቸው ሶስት የግንባታ አማካሪዎች፣ አስራ ሶስት የግንባታ ዲዛይንና የአስተዳደር አማካሪዎች፣ አስራ ሶስት የግንባታ ኮንትራክተሮች እንዲሁም አነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች በግንባታው እንዲሳተፉ ታቅዷል:: ጂ.ቲ.ዜድ. ከላይ ከተጠቀሱት የግንባታ ዲዛይንና የአስተዳደር አማካሪዎች በተጨማሪ ኮንትራክተሮችን የመቅጠርና የማሰናበት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

6. ፕሮጀክቱ ሲጀመር ትምህርት ሚኒስቴር ለእያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ አንድ አንድ ፕሮጀክት ማኔጀርና እንዲሁም በማዕከል ለሁሉም ዩኒቨርስቲዎች አንድ ማኔጀር እንደሚመደብ በውሉ ላይ ተገልጿል፡፡

   የፕሮጀክት ማኔጀሮቹ ሚና ግንባታው በሚከናወንባቸው ቦታዎች በመገኘት ትምህርት ሚኒስቴርን በመወከል ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ መስጠት

   ነው፡፡

   የግንባታ ክንውኖችን ደረጃ በተመለከተ ጂ.ቲ.ዜድ. የአስራ ሶስቱም ዩኒቨርሰቲዎች ፕሮጀክት ማኔጀሮች ባሉበት በየወሩ አስፈላጊውን የሥራ ግምገማ በማድረግ ለትምህርት ሚ/ር ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት ከትምህርት ሚ/ር ጋር ተስማምቷል፡ ፡

7. በኮንትራክት ሰነዱ መሠረት፣ ጂ.ቲ.ዜድ. የግንባታ ደረጃ ክትትልና የሂሳብ ማስታወቂያዎችን በማዘጋጀት በየሶስት ወሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርም በሪፖርቶቹ በሚመለከቱት የማሻሻያ ሃሣቦች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለበት፡፡

<u>የገንዘብ አከፋፈል</u>

8. ጂ.ቲ.ዜድ. ስራውን ለማከናወን ብር 1,908,848,931 እና ዩሮ 59,407,975 ለመቀበል ተስማምቷል፡፡ ጂ.ቲ.ዜድ ስምምነቱን የተዋዋለው በነሐሴ 1997 ዓ.ም. ነው፡፡ አከፋፈሉም ፤

- ግንባታው ሲጀመር 8% ብር 152,707,914 እና ዩሮ 4,752,638
- ለሚቀጥሉት 47 ወራት በየወሩ ብር 36,554,923 እና ዩሮ 1,141,064 (በድምሩ ብር 1,718,081,375 እና ዩሮ 53,630,006)
- ለቀሪው የዋስትና ጊዜ 12 ወራቶች በየወሩ ብር 1,899,071 እና ዩሮ 45,839 (በድምሩ ብር 22,788,850 እና ዩሮ 550,067) ነው፡፡
- የመጨረሻው ክፍያ ደግሞ ብር 15,270,791 እና ዩሮ 475,264 እንደሚሆን በኮንትራት ሰነዱ ውስጥ ተገልጿል፡፡

<u>ዕቃ ግዢ</u>

9. የሚተከሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንዲሁም የላብራቶር ዕቃዎች ግዥን በተመለከተ ጂ.ቲ.ዜድ በዕቅዱ መሰረት የሚያጠናቅቃቸውን ሕንፃዎች ለትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ማስፋፊያና ማጠናከሪያ አገልግሎት መምሪያ ያሳውቃል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ ግዢው እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡ ክፍያው ከተፈፀመ በኋላ የተገዛውን ንብረት ዩኒቨርስቲዎቹ እንዲረከቧቸው ይደረጋል፡፡

<u>የዩኒቨርስቲ አቅም ግንባ ፕሮግራም ዋና ዋና ዓላማዎች</u>

10. በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ ፕሮግራሙ የሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች እንዳሉት ተገልጿል፡፡

- በቂ ባለሙያ በማፍራት የኢትዮጵያን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዘመናዊና በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ እና፣

- በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ አሥራ አምስት ከተሞች አስራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች በአስራ አምስት ቦታ ማለትም በዲላ፣ በሶዶ፣ በሚዛን ተፈሪ እና ቴፒ፣ በነቀምቴ፣ በድሬዳዋ፣ በጅጅጋ፣ በደሴ እና ኮምቦልቻ፣ በሰመራ፣ በደብረማርቆስ፣ በደብረብርሃን፣ በሮቤ፣ በአክሱም፣ እና በአዳማ በተሻለ ጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በአጭር ጊዜ ማስገንባት ነው፡፡

<u>የፋይናንስ ምንጭ</u>

11. ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህንን ኘሮግራም ለማስፈጸም ከመንግሥት ብር 1,908,848,930 እና ዩሮ 59,407,975 ተመድቧል፡፡ ዕቃ ግዢን በተመለከተ፤ በ2000 በጀት ዓመት የታወጀ በጀት ብር 1,777,307,000 እና በ2001 በጀት ዓመት ደግሞ ብር 92,247,800 ወጪ መሆኑ ይታወቃል፡፡

<u>የኦዲቱ አላማ</u>

12. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ፣ የከፍተኛ ትምህርት በሃገሪቱ እንዲዳረስ ለማድረግ በመንግሥት በተለያዩ ክልሎች በመገንባት ላይ ያሉት አስራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች በተያዘላቸው መርሃግብር መሠረት መከናወናቸውን እና የዩኒቨርሲቲዎቹ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የግ አፈጻጸም ስርዓት አጥጋቢ መሆኑን በማረጋገጥ፣ እንዲሁም ችግሮችም ካሉ ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሣቦችን ለመስጠት ነው፡፡

<u>የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

13. ለዝርዝር ኦዲቱ ተስማሚ የሆኑ የሚከተሉት ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡

እነሱም፤

I. የከፍተኛ ትምህርት ተkማትን ለማስፋፋት በመሰራት ላይ ያሉትን የአስራ ሶስት ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ እቅድ አፈጻጸም አጥጋቢ መሆኑን እንዲሁም የግንባታ ደረጃው እና የገንዘብ ክፍያው በእቅድ፣ በደንብ መመሪያ መሰረት የተከናወነ መሆኑን መገምገም እና
II. የከፍተኛ ትምህርት ተkማትን ለማስፋፋት በመሰራት ላይ ላሉት አስራ ሶስት ዩኒቨርስቲዎች የትምህርት መርጃ ዕቃዎች ግዥ አፈፃፀምን መገምገም

የሚሉ ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Auditing Standards) እና የክዋኔ ኦዲትን በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 68/1989 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡

## <u>የመመዘኛ መስፈርቶች</u>

14. ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ ከትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊዎች ጋር ውይይት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ የዚህ ሪፖርት አባሪ ሆነው ተያይዘዋል፡፡

/አባሪ 1/

## <u>የኦዲቱ ዘዴ</u>

15. ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን ከአቅም ግንባታ ሚኒስቴር፣ ከጂ.ቲ.ዜድ እንዲሁም ከአሥራ ሦስቱ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በናሙና ከተመረጡ ስድስት ዩኒቨርሲቲዎች ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በዩኒቨርሲቲዎቹ በመማር ላይ ካሉ ተማሪዎችና የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ እንዲሁም ከኮንትራክተሮች ለኦዲቱ ሥራ የሚያስፈልጉ የፅሁፍና የቃል መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## <u>የኦዲቱ ወሰን</u>

16. የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ሶስት በጀት ዓመታትን ማለትም ከ1999-2001 ያለውን አሰራር ነው፡፡ ፕሮግራሙ ሁለት ዋና ዋና አላማዎች ያሉት ቢሆንም "ብቁ ባለሙያ በማፍራት የኢትዮጵያን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዘመናዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የማድረግ" የሚለው አላማ በኦዲቱ አልተካተተም፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### የዩኒቨርስቲዎቹ የፕሮጀክት ቀረፃና እቅድ አፈፃፀም

#### የአዋጪነት ጥናት ስለ አለመከናወኑ

17. በኦዲቱ ወቅት ፕሮጀክቱ ሲጀመር ግንባታው የሚከናወንባቸው ቦታዎች ያለውን የማቴሪያል አቅርቦት፣ ብቃት ያለው የሰው ሀይል መኖሩን፣ የትራንስፖርት አመቺነት እንዲሁም በአጠቃላይ ግንባታው በታሰበው ጊዜ፣ ገንዘብና የጥራት ደረጃ ለማከናወን የሚቻል መሆኑን ለመገምገም የሚያስችል የአዋጭነት ጥናት አለመደረጉ ለማወቅ ተችሏል፡

18. በዚሁ መሠረት ዩኒቨርስቲዎቹ በሚገነቡባቸው ከተማዎች ውስጥ በሶዶ ከተማ በቂ ውሀ እንደሌለ፣ በቴፒ የመንገድና የግንባታ ሠራተኞች ችግር መኖሩ፣ በተጨማሪም አሸዋና ድንጋይ ከአጎራባች ክልል ከጋምቤላ የሚመጣ መሆኑ፣ በሚዛን ተፈሪ እንዳንዴ በዓመት ውስጥ ያለማቋረጥ ለ8 ወራት የሚዘንብ እንደሆነ፣ በአዳማና በደብረ ብርሃን ከተሞች ደግሞ የቀን ሠራተኛ እጥረት እንዳለ በኮንትራክተሮች ተገልጿል፡፡

19. የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሰጡት ማብራሪያ ከመነሻው ስራውን መስራት የተመረጠው አዋጭነት ጥናት ተጀምሮ በቅደም ተከተል ይሰራል ከሚለው የተለምዶ አሰራር የተለየ መሆኑን ገልፀው ይህ አካሄድ አምስት ዓመታት አካባቢ ሊወስድ የሚችል በመሆኑ በእነዚህ አመታት ምንም አይነት የተማሪ ቅበላ እንዳይኖር የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

20. በመሠረቱ አንድ ፕሮጀክት ከመከናወኑ በፊት የአዋጭነት ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ ዩኒቨርስቲዎቹ በመጀመሪያ በተመረጡ ክልሎችና ዞኖቹ እንዲሠሩ ከተወሰነ በኋላም ቢሆን በአካባቢው፣ ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይገባ ነበር፣ ይኸም ባለመደረጉ ለፕሮጀክቱ ተጨማሪ ወጪ አስከትሏል ለግንባታው መዘግየትም አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶችና ኃላፊዎች በእቅድ-ዝግጅት ላይ ስለነበራቸው ተሳትፎ

21. የአስራ ሶስቱ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶች ስለሆኑ በዕቅድ-ዝግጅት ላይ ሊሳተፉ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በተካሄደበት ወቅት የዩኒቨርስቲዎቹ ፕሬዝዳንቶችና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በእቅድ ዝግጅቱ ወቅት እንዳልተሣተፉ ታውቋል፡፡

22. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች፣ ስለሁኔታው ተጠይቀው የዩኒቨርሲቲዎቹ ፕሬዝዳንቶችና ኃላፊዎች በዕቅድ ዝግጅቱ እንዲሳተፉ ያልተደረጉት ዕቅዱ በተዘጋጀበት ጊዜ የዩኒቨርቲዎቹ ግንባታ ባለመጀመሩና የዩኒቨርሲቲዎቹ ኘሬዝዳንቶችና ኃላፊዎች ባለመመደባቸው እንደሆነ ፕሬዝዳንቶቹ ከተሰየሙ በኋላ በየሳይቱ በጋራ በሚደረግ ክትትል እንዲሁም በት/ም ሚ/ር በሚደረጉ ግምገማዎች እንዲሣተፉ እንደተደረገ ሆኖም አፈጻፀሙ የተሟላና እና ተከታታይ እንዳልነበረ ገልፀዋል፡፡

23. የዩኒቨርሲቲው ኘሬዝዳንቶችና ኃላፊዎች ሥራ ከጀመሩ በኋላ በእቅድ ዝግጅቱ ቢሳተፉ ኖሮ በግንባታው ውስጥ መካተት የሚገባቸው ክፍሎች በሙሉ መካተታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ለግንባታዎቹ ጥራት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር፡፡የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶች ሥራ ከጀመሩ በኋላ በእቅድ ዝግጅት ባለመሳተፋቸው ምክንያት የአካዳሚና የአስተዳደር ቢሮዎች በግንባታ ውሉ ላይ አልተካተቱም፡፡ በዚህም ምክንያት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩን የዩኒቨርሲቲዎቹ ኃላፊዎች ተገልፀዋል፡፡

## የኃይል፣ የውሃ አቅርቦት እና ቴሌኮሙኒኬሽንን በተመለከተ ስለተደረገ ዝግጅት

24. ግንባታዎቹ ከመጀመራቸው በፊት ከውሃ ልማት፣ ከኤሌክትሪክ ሃይልና ከቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅቶች ጋር ለፕሮጀክቶቹ ማስፈጸሚያ እና ለዘለቄታ በቂ የሆነ የሀይል ምንጭ ፣ የውሀ አቅርቦትና የስልክ አገልግሎት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር በቅድሚያ ስምምነት እንዳላደረገ የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡ በናሙና ኦዲት ከተደረጉ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በአዳማ፣ በዲላ፣ በሶዶና በቴፒ ከፍተኛ የውሃ ችግር መኖሩ፣ በመደወላቡ ዩኒቨርስቲ አንድ የስልክ መስመር ብቻ እንዳለ እንዲሁም በደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ የኤሌክትሪክ ስርጭት ችግር መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከዩኒቨርስቲዎቹ ፕሬዘዳንቶችና ከተማሪ ተወካዮች ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ፕሮጀክቱ ከመተግበሩ በፊት ከላይ ከተመለከቱት መስሪያ ቤቶች ጋር ለምን ስምምነት እንዳልተደረገ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ ስምምነቱ እንዳልተደረገ ቢሆንም የቅድሚያ ስምምነቱ ባለመደረጉ ምክንያት ያገጠመ ችግር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

27. ሆኖም ከላይ እንደተመለከተው በተለያዩ ዩኒቨርስቲናዎች የውሃ፣ የኤሌክትሪክ ስርጭትና የስልክ ችግር በመፈጠሩ የተሰጠውን ምክንያት ለመቀበል ያስቸግራል በተጨማሪም ለውኃ፣ ለኃይልና ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች፣ ቅድሚያ ዝግጅት ያለመደረጉ ለግንባታ ሥራዎች መጓተት አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ በዩኒቨርስቲዎቹ ማህበረሰብ፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

### ስለ ተማሪዎች ማደሪያ ሕንጻዎች ዲዛይን

28. በኦዲቱ የሥራ ጉብኝት ወቅት ለደብረ ብርሀን ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማደሪያ የተሠራው ሕንጻ መስኮት ክፍት በመሆኑ የአካባቢውን ቀዝቃዛ አየር ለመቋቋም እንደማያስችል እንዲሁም የቴፒ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሕንጻ ደግሞ በአካባቢው በየጊዜው ከሚከሰተው የወባ ወረርሽኝ በሽታ አንጻር የወባ ትንኝ መከላከያ እንዳልተሠራለት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

29. የሚ/ር መ/ቤቶቹ ኃላፊዎች በአካባቢዎች ተስማሚ የሆነ የሕንጻ ዲዛይን ለምን እንዳልተሠራ ተጠይቀው ዩኒቨርስቲዎቹ ለሚገነቡባቸው አካባቢዎች ተስማሚ የሆኑ ሦስት ዓይነት ዲዛይኖች እንደተዘጋጁ ሆኖም እነዚህ ችግሮች በጊዜው እንዳልታዩ አብራርተው ችግሮቹን ለማስወገድ የማስተካከያ ሥራዎች

እንደሚሠሩ ገልፀዋል፡፡ ዲዛይኖቹ ሲሰሩ ከላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት ነበረባቸው፡ የማስተካከያ ሥራዎቹ በአስቸኳይ ካልተሠሩ ተማሪዎቹ ለተለያዩ በሽታዎች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

<u>የወባ ትንኝ መከላከያ ያልተሠራለት የቴፒ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ማደሪያ መስኮቶች</u>



**ስለግንባታ ዲዛይን ለውጥ፣**

30. በተገነቡት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በመጀመሪያ የተሰሩት 12 ብሎኮች (lot 1A) የፍሳሽ ችግር ማምጣታቸው ታውቋል፡፡ በናሙና ከተመረጡት ስድስቱ ዩኒቨርስቲዎች በመጀመሪያ የተሰሩት 12 ብሎኮች (lot 1A) መፀዳጃ ቤቶች ያለአገልግሎት እንደተዘጉና በተጨማሪ ወጪ የማስተካከያ ስራ እንደተሰራላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ግንባታው የዲዛይን ለውጥ እንዳያስከትል ጥንቃቄ ለምን እንዳልተደረገ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፤ የዲዛይን ማሻሻያ እየተሠራላቸው ያሉት ዋነኛ ቦታዎች የውሃ መፋሰሻ ስፍራዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ችግሮች ሊከሰቱ የቻሉት ዲዛይኖቹ ከጋራ መኖሪያ ቤቶች ዲዛይኖች ጋር ተመሣሣይ በመሆናቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጋራ

መኖሪያ ቤቶች የሚጠቀመው ሰው አነስተኛ ሲሆን የዩኒቨርስቲዎቹ ሕንጻዎች ተጠቃሚ በርከት ያለ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

32. የግንባታው ዲዛይን በየጊዜው ለውጥ እንዳያስከትል በቅድሚያ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባ ነበር፡፡ የዲዛይን ለውጥ መደረጉ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆኑም በላይ በተማሪዎቹ ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡

## የዩኒቨርስቲው ግንባታ የአፈፃፀምና የክትትል ስርአት

### ስለ የፕሮጄክት ማኔጀሮች ምደባ

33. ነሐሴ 1997 በትምህርት ሚ/ር እና በጂ.ቲ.ዜድ. በተደረገው የግንባታ ውል መሰረት ለክትትልና ለቁጥጥር ይረዳ ዘንድ ትምሕርት ሚኒስቴር ለጠቅላላው ፕሮጀክት አንድ ለየግንባታው ሳይት ደግሞ አንድ ፕሮጀክት ማኔጀር መመደብ ነበረበት፡፡

34. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለጠቅላላው ፕሮጀክት አንድ ማኔጀር የተመደበ ቢሆንም፣ ለዩኒቨርስቲዎቹ ግን በውሉ መሰረት አንድ፣ አንድ ማናጀር አልተመደበም፡ የት/ሚ/ር ኃላፊዎች ማኔጀሮቹ ለምን እንዳልተመደቡ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ ማኔጀር በየኘሮጀክቶቹ እንዲቀመጥ በስምምነቱ ውስጥ ተካቶ የነበረ ቢሆንም ከአሰራር አኳያ የፕሮጀክቱን አስተዳደር የሚያከናውነውን አካል ከትምህርት ሚኒስቴር ሙያው የተሻለ አቅም ኖሮት በሚወከል ባለሙያ ለመቆጣጠር መሞከሩ በቅድሚያ ከገበያው አግኝቶ መመደብ አዳጋች ሲሆን ቢገኝም እንኳ የፕሮጀክት አስተዳደር ለሚያከናውነው ጂ.ቲ. ዜድ ኃላፊነቱንና ግዴታውን ለመወጣት የሚያስቸግር ሁኔታ እንደሚፈጥር በማገናዘብ ነው፡፡ ለዚህም በማዕከል አንድ አካል በመመደብ በሚቀርቡ ሪፖርቶች የክትትል ተግባር ሲከናወን እንደነበር በመውጫ ስብሰባ ገልፀዋል፡፡

35. ይሁን እንጂ በማዕከል አንድ አካል ተመድቧል የተባለው ሁኔታ ሲጣራ ከሰብሳቢው ማለትም ከሚኒስቴር ዴኤታው በስተቀር ሁሉም የጂ.ቲ. ዜድ ባልደረቦች በመሆናቸው ገለልተኛ አካል ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ እንዲሁም ባለሙያ ባለመመደቡ ጂ.ቲ. ዜድ ኃላፊነቱንና ግደታውን ለመወጣት የሚያስቸግር ሁኔታ ይፈጥራል የተባለው በኛ በኩል ተቀባይነት የለውም፡፡ ሌላው ደግሞ ከገበያ ባለሙያ የማይገኝ ከሆነ ከመነሻው ውሉ ውስጥ መካተት አልነበረበትም፡፡ በመሆኑም በውሉ ላይ በተጠቀሰው


መሠረት አላስፈላጊ መዘግየትን ለመከላከል የሚ/ር መ/ቤቱን የሚወክል ቡድን መመደብ ነበረበት፡፡

36. የክትትልና የቁጥጥር ተግባር የሚያከናውን ባለሙያ አለመመደቡ፣ ጂ.ቲ.ዜድ በትክክል ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ለመከታተልና ችግሮችም ቢፈጠሩ በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም ክፍያዎች ከግንባታው እድገት ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

**ስለግንባታው ጊዜ**

37. በነሐሴ 1997 (August 2005) በተደረገው ውል መሰረት በመስከረም 2002 (September 2009) ላይ የአስራ ሶስቱም ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ተጠናቆ አስራ ሶስቱም ዩኒቨርስቲዎች በ2003 ዓ.ም 121,000 ተማሪዎችን የመቀበል አቅም እንደሚኖራቸው ታቅዶ ነበር፡፡

38. ይሁን እንጂ በመስከረም 2002 (በSeptember 2009) የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት መሰረት ግንባታው የሚገኝበት ደረጃ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥና ግራፍ መሰረት ስራው በጣም እንደተጓተተ ተመልክቷል፡፡ በአጠቃላይ ግንባታው በአማካኝ 50 % ብቻ ተጠናቆ ተገኝቷል፡፡



39. የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች መረጃው ትክክል እንደሆነ ለስራው መዘግየት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ፤ የግንባታ ዕቃ አቅርቦት እጥረት፣ በትንሽ ትርፍና የወጪ መጠን ምክንያት የስራ ተkራጮች ስራውን ለመስራት አለመፈለጋቸው የኃይልና የውሃ እጥረት እንዲሁም የግንባታ ሰራተኞች ያለመገኘት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውንም ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ያጋጠሙ ችግሮችን በመዳሰስ የፕሮጀክቱ መጠናቀቂያ ጊዜ እስከ ታህሳስ 2003 ዓ.ም እንዲራዘም ስምምነት እንደተደረገ አብራርተዋል፡፡

40. ነገር ግን ከኃይልና ከግንባታ እቃዎች እጥረት ችግሮች በስተቀር የተቀሩት ችግሮች በቅድመ ግንባታ ጥናት ወቅት መታወቅ የነበረባቸው ስለነበሩ የቀረቡት ምክንያቶች አሣማኝ ሆነው አልተገኙም፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት የተሰራው ስራ የ50% ሆኖ ሳለ በሚቀጥለው አንድ ዓመት ቀሪው 50% ስራ ይጠናቀቃል ብሎ መገመትም ያዳግታል፡ ፡ የግንባታው እድገት አዝጋሚ መሆን የተማሪ መቀበያን ጊዜ በማዘግየት በአካዳሚ ፕሮግራሙ ላይ መዛባትን አስከትሏል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎችን እና መምህራንን ያለ በቂ እረፍት እንዲሰሩ ከማድረጉም በላይ ዩኒቨርስቲዎችም ለመምህራን ተጨማሪ ሰዓት ክፍያ እንዲከፍሉ አድርጓል፡፡እንዲሁም እ.ኤ.አ 2009 የትምህርት ዓመት የተማሪ የመቀበል አቅም (ክንውን) (55,842) ሲሆን የታቀደው ግን (97,500) ነበር፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርስቲዎች የመቀበል አቅም በ43% ዝቅ እንዲል ምክንያት ሆኗል፡፡

## ከተማሪ ቅበላ በፊት መከናወን ስለነበረባቸው ስራዎች

41. ከተማሪ ቅበላ በፊት፣ ዩኒቨርስቲዎቹ ሲሰሩ የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያግዙ የመማሪያ፣ የማደሪያ፣ የቤተመፅሃፍት፣የላቦራቶሪና የመፀዳጃ ቤቶች እና የመሳሰሉት መሟላት ይኖርባቸዋል።

42. ሆኖም በናሙና ከታዩት ስድስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ሶስቱ፣ ማለትም የሚዛን፣ቴፒ የመደውላቡና የዲላ ዩኒቨርስቲዎች የሳይንስ ፋክልቲዎች የላብራቶሪ መሳሪያ ስለሌላቸው ተማሪዎች ወደተለያዩ ክልሎች በመሄድ ለነባር ዩኒቨርስቲዎች ክፍያ በመክፈል ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል።

43. ከዚህም ሌላ ለዩኒቨርስቲዎች የተሰሩት ጊዚያዊ መፀዳጃ ቤቶች በአማካኝ ለ800 ተማሪዎች የተገነቡ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከ3000 ተማሪዎች በላይ እያስተናገዱ

እንደሚገኙ ታውkል፡፡ የተጠቃሚዎቹ ቁጥር በጣም ከፍተኛ በመሆኑ የመደወላቡ ዩኒቨርስቲ መፀዳጃ ቤት ሞልቶ ግቢውን መሀል ለመሀል እያkረጠ የሚፈስ ሲሆን በጠቅላላው እነዚህን መፀዳጃ ቤቶች በጊዜያዊነት ለማሰራትም ከአስራ ሶስቱ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ለሰባቱ ብር 5,294,261.70 ወጪ ሆኗል፡፡

44. በቴፒና በመደወላቡ ዩኒቨርስቲዎች ለቤተ መጻሕፍት የተሰሩ ህንፃዎች ለምግብ አዳራሽነት እንዲያገለግሉ በመደረጋቸው በቤተ-መጽሀፍት አጠቃቀም ላይ ችግር ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎቹ ማደሪያ ለአራት ተማሪዎች የተሰራ ሲሆን ስድስት ተማሪዎችን እንዲያስተናግዱ በመደረጉና ለሁለት ተማሪዎች የእቃ ማስቀመጫ ሎከር የሌለ በመሆኑ ለተማሪዎቹ እና ለእቃቸው ደህንነት ምቹ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**የተማሪዎቹ ማደሪያ ለአራት ተማሪዎች የተሰራ ሆኖ ሳለ ለስድስት ተማሪዎች እንድያገለግል መደረጉ፣**



44. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በግንባታው መዘግየት ምክንያት ችግሩ የተከሰተ ቢሆንም ግንባታው ሲጠናቀቅ የተገለጹት ችግሮች በሙሉ እንደሚወገዱ ገልጸዋል፡

የግንባታው እድገትና የሚገቡት ተማሪዎች ብዛት ባለመጣጣሙ የትምህርት ሚ/ርን ለተለያዩ ተጨማሪ ወጪዎች ዳርጓል፡፡ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይም ችግር ፈጥሯል፡፡

## የመረጃ አያያዝና ክትትል ስርአት

### የግንባታውን ወጪ በተሟላ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ያለመኖሩ

45. ትምህርት ሚ/ር ለዩኒቨርስቲዎቹ ማሰሪያ የሚከፍለውን ወጪ፤የወጪውን አይነት የገንዘቡን ልክ፣የግንባታውን ደረጃ እንዲሁም ጊዜውን የሚያሳይ መቆጣጠሪያ መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጂ.ቲ.ዜድ የራሱን አፈፃፀም ሪፖርቶች የሚያቀርብ ቢሆንም ት/ሚ/ር እራሱ የሚያዘጋጃቸው መረጃዎች እንደሌለው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ጂ.ቲ.ዜድ የሚያቀርብልን የግንባታ፣ የስራ ማስኬጃ፣ የአቅም ግንባታ እና የፕሮጀክት ክፍያ ወጪዎችን እንይዛለን፣ ይህን አስመልክቶ የማመሳከር ስራ ባሁኑ ወቅት እስከ 2008 ድረስ ያለው የተሰራ ሲሆን የ2009 በቀጣይነት እንሰራለን ብለዋል፡

47. ማስረጃዎች በት/ም ሚ/ር ተሟልተው ያለመያዛቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የግንባታውን ወጪ በአይነት፣ በጊዜና በገንዘብ መጠን የሚያሳይ ዝርዝርና የተሟላ መረጃ በትምህርት ሚ/ር አለመያዙ ፕሮጀክቶችን በሚገባ ለመቆጣጠር አያስችልም፡፡

### በህንፃዎች ላይ ስለደረሱ ጉዳቶች

48. በናሙና ከታዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ፤ በሶዶ ዩኒቨርስቲ በአስራ አምስት ህንፃዎች ውስጥ ጎርፍ የገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሚዛን ቴፒ የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃዎች ውስጥ የ980 በሮች ማጠፊያቸውና ቁልፋቸው እንደተሰበረ ለማወቅ ተችሏል ፡፡ በአዳማ የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃ ውስጥ የ660 የበር ቁልፎች ችግር ያለባቸው ለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

49. የመ/ቤቱ ኃላፊዎች የጎርፍ ችግሩ ሊከሰት የቻለው ተkራጩ አስፈላጊው ክትትልና ስራ ባለማከናወኑ ምክንያት መሆኑንና፣ kሚ የሆነ የጎርፍ መከላከያ ስራ ሲሰራ ችግሩ እንደሚፈታ ገልፀዋል፡፡የቁልፍ ችግሮቹን በተመለከተ ደግሞ የተገጠሙት ቁልፎች ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ተስማሚ የሆኑ ነበሩ፡፡ በዩኒቨርስቲዎች ግን ተጠቃሚዎች ስለበዙ የቁልፎቹ የአገልግሎት ጊዜ ሊያጥር ችሏል፡፡ ስለሆነም ለወደፊቱ የተጠቃሚ ብዛትን መሠረት ባደረጉ ቁልፎች እንደሚተኩ አብራርተዋል፡፡

50. በአብዛኛዎቹ ዩኒቨርስቲዎች ከጊዜያዊ ርክክብ በኂላ በአያያዝ ጉድለት የሚከሰቱ ጥፋቶችን ተከታትሎ ለመጠገን የሚችሉ የጥገና ስራ ክፍሎች ባለመኖራቸው ችግሮቹ ሊባባሱ ችለዋል፡፡

51. ህንፃው ከተገነባ በኂላም ሆነ በግንባታው ወቅት ጉዳት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል፡፡ የግንባታው ችግሮች በወቅቱ እንዲታረሙና የሚመለከተው ክፍል እንዲያውቀው ካልተደረገ ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡ በተለይም የጎርፉ ችግር ከቀጠለ ሕንፃውን ለከፍተኛ ጉዳት ሊዳርገው ይችላል፡፡

**ስለዕቃ ግዥ**

52. በኦዲቱ ወቅት ለአስራ ሶስቱ ዩኒቨርስቲዎች አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ዕቃዎች ግዥ የሚፈፀመው የዩኒቨርስቲዎቹ የግንባታ ደረጃ እየታየ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡

53. በዚሁ መሰረት በናሙና ከታዩት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ለወጥ ቤት የተገዙ እቃዎች (Kitchen Equipment) በብር 2,726,757.17 (ሁለት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ከአስራ ሰባት ሳንቲም) እና በብር 1,256,492.29 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ሁለት ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) የተገዛ የፎቶ ኮፒ ማባዣ ያለአገልግሎት ተቀምጠዋል፡፡

54. ለዲላ ዩኒቨርስቲ የተሰሩ ቁምሳጥኖች የሚገጠሙበት ግድግዳዎች ጠባብ በመሆናቸው ተሰርተው የመጡ ቁምሳጥኖች እንደገና እንዲስተካከሉ ወደ ፋብሪካ የተላኩ መሆኑ፤

ለሶዶ ዩኒቨርስቲ አራት ህንፃዎች በስፔስፊኬሽን መሰረት ህንፃዎቹ የቁምሳጥን ማስገቢያ ስላልተሰራላቸው ህንፃዎቹ እንደገና እንዲስተካከሉ የታዘዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

55 ለመደወላቡ እና ለሶዶ ዩኒቨርስቲዎች የተገዙ የላብራቶሪና የምግብ ቤት እቃዎች

ግንባታው ባለመጠናቀቁ ምክንያት ለአንድ አመት ያለአገልግሎት በመጋዘን ውስጥ እንደተቀመጡ ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. ስለዚህ ጉዳይ ኃላፊዎቹ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የጥድፊያ ጊዜ ስለነበር በመጀመሪያ የተሠሩት ቁም ሣጥኖች በስፔስፊኬሽን / Specification / መሠረት አልነበረም፤ በኋላ ግን እንዲስተካከል ተደርጓል ብለዋል፡፡ እቃዎችንም ግዥ በተመለከተ በወቅቱ የአሠራር ክፍተት እንደነበር ገልፀዋል፡፡

57. የግንባታውን የስራ ዕቅድና ፕሮግራም ያገናዘበ ግኘ ሊኖር ይገባል። የግኘውና የግንባታው እቅድ አፈፃፀም ያልተጣጣመ መሆን ተገዝተው የሚመጡ ዕቃዎች አመቺ ባልሆነ ቦታ ተቀምጠው ለብልሽት እንዲጋለጡ ሊያደርግ ይችላሉ ።

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

58. አስራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎችን በተለያዩ ክልሎች በተመጣጣኝ ወጪና በአጭር ጊዜ ለመገንባት የተቀመጠው ዓላማ ገንቢ እንደነበር እንገነዘባለን፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግሥት የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም በተመጣጣኝ ወጪና በቀልጣፋ ሁኔታ መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንጻር የፕሮጀክቶች አፈጻፀም በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

59. የአዋጭነት ጥናት ላለመደረጉ የተሰጠው ምክንያት በከፊል አሣማኝ ቢሆንም ዩኒቨርስቲዎቹ የሚሠሩበት ቦታ ከተወሰነ በኋላም ቢሆን ቢያንስ ለግንባታ የሚሆን ግባት መኖሩ ባለመረጋገጡ ለዩኒቨርስቲዎቹ የግንባታ ሥራ መጓተት ከፍተኛ አስዋጽኦ አድርጓል፡፡

60. ከተማሪዎች ቅበላ በፊት መሟላት የነበረባቸው እንደ ተማሪዎች ማደሪያ፤ቤተ-መፅሐፍትና የላብራቶሪ መሳሪያዎች እንዲሁም የውሃ፤ የመብራት፤ የመፀዳጃ አገልግሎት ባለመሟላታቸው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደሩ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

61. በእኛ አስተያየት በዩኒቨርስቲዎቹም መመደብ የነበረባቸው የፕሮጀክት ማናጀሮች ባለመመደባቸው ለግንባታዎች መጓተት ከዋና ዋናው ምክንያቶች አንዱ ከመሆኑም በላይ በየፕሮጀክት ሳይቱ የሚያጋጥሙ ችግሮች በወቅቱ እንዳይፈቱ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

62. ለጋራ መኖሪያ ቤቶች የዋለው ዲዛይን ለዩኒቨርስቲዎቹ ግንባታ በመዋሉና የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ ተጨማሪ ወጪ አስከትሏል፡፡ በቅድሚያ ጥንቃቄ ያለመደረጉም ተገቢ ሆኖ ተልተገኘም፡

63. በአጠቃላይ ግንባታዎቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብና ወጪ ሊጠናቀቁ ባለመቻላቸው በመጀመሪያ የተቀመጠውን የዩንቨርስቲዎችን የመቀበል አቅም በ43% ዝቅ እንዲል ምክንያት ሆኗል፡፡ ቀሪውን ግንባታ ለማጠናቀቅ የሚፈጀው ጊዜና የሚያስፈልገውም ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ከግንባታዎቹ መጀመር በፊት የተደረገው ቅደም ጥናትና ጥንቃቄ በቂ እንዳልነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

በክፍል ሁለት የተመለከቱ ድክመቶችን ለማስወገድ እና እንዲሁም ወደፊት ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ከዚህ የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ተግባር ላይ ቢውሉ ጠቃሚ ናቸው ብለን እናምናለን፡፡

- ❖ ወደፊት የሚሰሩት ዩኒቨርሲቲዎች ከመገንባታቸው በፊት የአዋጭነት ጥናት እንዲካሄድ እንዲሁም ግንባታው ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ጋር በመነጋገር ቅድመ-ዝግጅት እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡
- ❖ የሕንፃዎች ግንባታ ዲዛይን ከአካባቢው የአየር ሁኔታና የመሬት አቀማመጥ ተስማሚ መሆኑን መረጋገጥ ይኖርበታል፤
- ❖ የሕንፃው ስራ የተጓተተ በመሆኑ፤ አሁንም በተራዘመው የጊዜ ገድብ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህንንም የቁጥጥር ስራ ለማካሄድ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በውሉ መሰረት አንድ የፕሮጀክት ማኔጀር መመደብ ያስፈልጋል፡፡ ይኸ የማይቻል ከሆነ ጂ.ቲ.ዜ.ድ አባል ያልሆነበት ነጻ አካል አቋቁሞ የፕሮጀክቶቹን የሥራ ሂደት በመቃኘትና በመገምገም ለሚ/ር መ/ቤቱ አመራር ወቅታዊ ሪፖርት እንዲያቀርብ መደረግ አለበት፡፡
- ❖ የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንቶችና ከፍተኛ ኃላፊዎች ግንባታውን በተመለከተ በየጊዜው በሚደረጉ ስብሰባዎችና ግምገማዎች ላይ በተሟላ ሁኔታ እንዲሳተፉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

  የግንባታ ስራዎች የስራ ሂደቶችን በአይነት፤ በመጠን፣ በጊዜና በገንዘብ ልክ የሚያሳይ መቆጣጠሪያ መዝገብ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- ❖ ከተማሪዎች ቅበላ በፊት ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ማለትም ላብራቶሪ፤ ቤተ-መፅሐፍት፤ የመመገቢያና የማደሪያ ሕንፃዎች ሊሟሉ ይገባል፤ አሁንም ቢሆን እነዚህ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ ተገቢው ጥረት መደረግ ይኖርበታል፤

- ለዩኒቨርሲቲዎች ልዩ ልዩ ሕንፃዎች የሚገዙ የመገልገያ ዕቃዎች ብልሽት በሚደርስባቸው ጊዜ አስፈላጊውን ጥገና የሚያደርግ ክፍል በየዩኒቨርሲቲዎቹ ሊቋቋም ይገባል፤
- ለጊዜያዊ መፀዳጃ ቤቶች የሚወጣውን ወጪ ለመቀነስና በመፀዳጃ ቤቶች የሚታየውን ችግር ለማስወገድ በተቀየረው ዲዛይን መሰረት ቋሚ መፀዳጃ ቤቶች በአስቸኳይ መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡
- የግንባታውን የሥራ ዕቅድና ኘሮግራም ያገናዘበ ግዥ ሊፈፀም ይገባል፡፡
- የኘሮጀክቶቹ የሥራ ሂደት ውስብስብ በመሆኑ የእያንዳንዱን አካል ተጠያቂነትን የሚያጠነክር አሠራር መዘርጋት አለበት፡፡ ተጠያቂነትን ለማጠናከር ለእያንዳንዱ አካል የማያሻማ ኃላፊነትና የሥራ መዘርዝር መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የትምህርት ሚ/ርና የስድስቱ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም የጂ.ቲ.ዜድ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስላደረጉልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

የከለሰው፡- ሙሉጌታ ተሰማ

ሡልጣን መሐመድ

ኦዲተሮች፤-

ወርቃፈራሁ ወንድሙ -------------

ሜልኮል ኃ/ጊዮርጊስ ----------------

ሚለን አማረ -----------------------

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| ተ.ቁ. | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| 1 | 1/ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት የፕሮጀክት ረቂቅ / Project proposal/ መቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ ፡- Condition of contract for works of civil engineering construction |
| | 2/ የዩኒቨርስቲው ግንባ ሲጀመር የሚመለከታቸው ሀላፊዎች በእቅድ ዝግጅቱ ላይ ሊሣተፉ ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 3/ ብዙ ሺህ ተማሪዎችን ለማስተናገድ የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ከውሃ ልማትሚ/ር፣ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ፣ ከቴለኮሙኒኬሽን ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ሥምምነት መደረግ አለበት፡፡ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 4/ ለእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ በአማካሪ መሀንዲሱ የሚቀርበው ኘላን /ዲዛይን/ በወቅታዊ የአየር ሁኔታና የመሬት አቀማመጥ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል፡፡ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 5/ የግንባታው ዲዛይን በየጊዜው ለውጥ እንዳያስከትል ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ የዲዛይን ለውጡ ዲዛይኑ በግንባ ስራ ከመዋሉ አስቀድሞ እንዲደረግ ለአማካሪ መሀንዲሱ ተገቢ መመሪያ ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 6/ ግንባታውን የሚያከናውነው ድርጅት ከግንባታው አካባቢ በተቻለ መጠን ሠፋፊና ከባድ እቃዎችን ከመንገድ ላይ በማንሳት ለመገናኛ የሚሆን አመቺ ሁኔታን መፍጠር ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ ፡- Condition of contract for works of civil engineering construction |
| | 7/ የግንባታዎቹ ደረጃ ከእቅዱ ጋር የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ |
| | 8/ በግንባታው ዘርፍ ሥራ ከብር 20,000,000 በላይ ለሆነ የግንባታ ሥራ ዓለም አቀፍ ጨረታ ሊወጣ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡- የመንግስት የግዥ መመሪያ |
| | 9/ የግንባታው ክፍያ /Construction cost\አከፋፈል ሥርዓት የግንባታውን እድገት ወይም ግንባታው በተጠናቀቀበት ልክ ሊሆን ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 10/ የግንባታው ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የክፍያ የምስክር ወረቀት ሊቀርብ ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፡- Condition of contract for works of civil engineering construction |

| ተ.ቁ. | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች |
|---|---|
| | 11/ ሚ/ር መ/ቤቱ ከጨረታ አሸናፊ ድRጅቶች ጋር ህጋዊ የኮንስትራክሽ የአማካሪነት ውል መፈራረም ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 12/ የሥራ ተቋራጮች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የገንዘብ አቅማቸው፣ የሰለጠነ የሰው ሀይል፣ የግንባታ መሣሪያዎችን ያሟሉ መሆናቸውንና በሌላ የግንባታ ስራ(ሣይት) ያልተጨናነቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ |
| | 13/ የግንባታው¿ ወጪ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጊዜና የገንዘቡን ልክ የሚያሣይ መቆጣጠሪያ ት/ሚ/ር መያዝ ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 14/ ከተማሪ ቅበላ በፊት መሟላት የሚገባቸው የተማሪ ማደሪያና መመሪያክፍሎችውሃ፣መብራት፣ቤተመጻህፍትና ላብራቶሪ መመገቢያ ቦታዎችና መፀዳጃዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 15/ የግንባታው ሂደት እንደ ፋክሊቲው የሚያስፈልገውን የመማሪያ፣ የማደሪያ እና የላብራቶር ህንፃዎችን ያሟላ የቅደም ተከተል አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 16/ መ/ቤቱ ለጠቅላላ ለ13ቱ ዩኒቨርስቲዎች አንድ ኘሮጀክት ማኔጀር እና በተጨማሪም ለእያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ አንድ አንድ ኘሮጀክት ማኔጀር ውሣኔ ለመስጠትና ለመቆጣጠር መመደብ አለበት፡፡<br>ምንጭ:- ከግንባታ ውል /construction agreement/ |
| | 16.1 ኘሮጀክት ማኔጀሮቹ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የግንባታ ሂደት ላይ የክትትል እና የግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው የበላይ አካል (ትምህርት ሚ/ር) ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ |
| | 16.2 በግምገማው ውጤት መሠረት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰዱን እየተከታተለ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ |
| | 17/ ሚ/ር መ/ቤቱ የግንባታውን የሥራ ሂደት በሚመለከት የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ደረጃቸውን በጠበቀና አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ከ13ቱ ዩኒቨርሲቲዎች ለመሰብሰብ እና ለማጠናቀር የሚያስችል አሠራር ሊኖር ይገባል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 18/ የሚ/ር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ከጂ.ቲ.ዜድ እና ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ የተነሱ ችግሮችም ሆነ የመ`ትሄ ሀሳቦች በሚ/ር መ/ቤቱ በቃለ-ጉባኤ ሊያዙና ሊጠበቁ ይገባል፡፡<br>ምንጭ :- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| ተ.ቁ. | የኦዲት መስፈርቶች |
| | 19/ ጂ.ቲ.ዜድ የግንባታውን ሂደት አስመልክቶ ለትምህርት ሚ/ር እና ለአቅም ግንባታ ወርሀዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ፣ የዘጠኝ እና አመታዊ ሪፖርት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ (good practice) |
| | 20/ ሚ/ር መ/ቤቱ ግንባታውን የሚቆጣጠርበትና የሚገመግምበት የኘሮጀክት አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል ይገባዋል፡፡ |

| | |
|---|---|
| | 21/ የዩኒቨርስቲዎቹ አስተዳደር የድርጊት መርሀ ግብር አዘጋጅቶ በግንባታው ምክንያት የተከሰተውን ችግር በተመለከተ ጥናት በማካሄድ መለየትና ችግሮቹንም ለመፍታት የሚያስችል የመፍትሔ ሃሣብ በማቅረብ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርበታል፡ ፡<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| 2 | 1. ሚ/ር መ/ቤቱ ለሚያከናውነው የቋሚና አላቂ የንብረት ግዥዎች የሚያገለግል ዝርዝር የሥራ መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 2. የግንባታውን የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም ያገናዘበ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት የሚከናወን የጥቅል ግዥ ሊኖር ይገባል።<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 3. ግዥ አገልግሎቱ የታዘዙ ዕቃዎችን ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የግዥ ሂደታቸው የተጠናቀቁ ግዥዎች እስታስቲካዊ መረጃ ተዘጋጅቶ ለወደፊቱ የግዥ ሂደቱን ሊያግዝ የሚያስችል ሥርዓት ሊኖር ይገባል።<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 4.በጨረታ ለሚገዙ ዕቃዎች የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ሊቋቋም ይገባል።<br>ምንጭ፡- የግ መመሪያ |
| | 5. የጨረታ ሂደት እና ግምገማ የሚጠናቀቅበት የተወሰነ የጊዜ ገደብ ሊኖር ይገባል።<br>ምንጭ፡- የግ መመሪያ |
| | 6. ከአንድ አቅራቢ ብቻ የሚገዙ ግዥዎች ከብቸኛ አቅራቢ አስቸኳይ ግዥ ፣ ግዥው የሚወስደው ጊዜ፣ የመለዋወጫው ዕቃ ከመሣሪያው አምራች አገር ብቻ መገኘቱ የሚሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል።<br>ምንጭ፡- የግ መመሪያ |
| | 7. የግዥ መረጃዎች ማለትም ከግዥ ጥያቄ አንስቶ በየደረጃው ግዥውን የሚመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ ፋይል ሊደረጉ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፣ ከመልካም ሥራ ተሞክሮ(good practice) |
| | 8. የዕቃ ግዥና ንብረት አስተዳደር ስራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ክፍሎች የተጣለባቸውን የስራ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት<br>ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |

| ተ.ቁ. | የኦዲት መስፈርቶች |
|---|---|
| | 9. በፕሮጀክት መልክ ተቀርጸው የሚከናወኑ ግዥዎች በተቀረፁበት ዓላማ እና ዕቅድ መሠረት በታቀደላቸው ወጪና የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊጠናቀቁ ይገባል። <br> ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ |
| | 10.አቅራቢ ድርጅቶች በውሉ መሠረት ሣያቀርቡ ቢገኙ እርምጃ ሊወሰድበት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ <br> ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 11.የሚፈፀመው የዕቃ ግዥ እንደ ቁምሣጥ፣ አልጋ፣ ወንበር የመሳሰሉት የሚተከሉ ዕቃዎች የግንባታውን ዲዛይን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። <br> ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 12.ትልልቅና የሚተከሉ ዕቃዎች ግዥው ከመፈጸሙ በፊት ተገቢ ቦታ ሊዘጋጅላቸው ይገባል ። <br> ምንጭ ፡- ከመልካም ሥራ ተሞክሮ (good practice) |
| | 13.የተገዙ ዕቃዎች ርክክብ በሚካሄድበት ጊዜ ዕቃዎች በትዕዛዝ መሠረት (Specification) ስለመገዛታቸው ሊረጋገጥ ይገባል። <br> ምንጭ፡- የግ መመሪያ |